Amharic | አማርኛ

# የሬድ ኖዝ የሀዘን እና የሰው ህልፈት/ማጣት ድጋፍ አገልግሎቶች

## ስለ ደረሰብዎ የሰው ህልፈት/ማጣት በጣም እናዝናለን ስለሆነም ልንረዳዎ እንፈልጋለን።

ሬድ ኖዝ እርግዝና በማስወረድ፣ ሙት በመውለድ፣ **በሕፃን ወይም በልጅ ሞት ምክንያት ለተጎዳ ወይም ተፅዕኖ ለደረሰበት ማንኛውንም ሰው ነፃ ድጋፍ ይሰጣል። ከሌሎች አንድ ዓይነት ወይም ተመሳሳይ ተሞክሮ ካላቸው ሰዎች ጋር እንዲገናኙ እንረዳዎታለን።**

**ሬድ ኖዝ ነፃ፣ ሚስጢሩ የጠበቀ አገልግሎት ነው። የሜዲኬር ካርድ አያስፈልግዎትም እንዲሁም የቪዛ ሁኔታ ምንም ይሁን ምን ድጋፍ እንሰጣለን።**

ሬድ ኖዝ ድጋፉን የሚቀይሰው የእርስዎ ፍላጎት መሰረት በማድረግ ነው። የተለያዩ የሙያ ድጋፍ አገልግሎቶችን እና የህይወት ልምድ ድጋፍ እንሰጣለን።

**የእንክብካቤ ቡድንዎ ወደ ሬድ ኖዝ ሪፈር አድርጎዎታል፣ ስለዚህ፡- ______________________________**

(የተላለፈበት/ሪፈር የተደረገበት ቀን)

የሬድ ኖዝ ቡድን አባል ይደውልልዎታል። ይህ ብዙውን ጊዜ በ24 ሰዓታት ውስጥ ይሆናል። ከአንድ ሰው ስልክ ካልተደወለልዎት፣ ሊደውሉልን ይችላሉ። ቁጥራችን **1300 308 307** ነው።

አፋጣኝ ድጋፍ ከፈለጉ ወደ **ነፃ የ24/7 የሀዘን እና የሰው ህልፈት/ማጣት የድጋፍ መስመራችንን በ 1300 308 307** መደወል፣ **ኢሜል peersupport@rednose.org.au** ማድረግ ወይም **www.rednosegriefandloss.org.au መጎብኘት ይችላሉ**

**የሁለት ቋንቋ ተናጋሪ የሆነ ደጋፊን ለማነጋገር መጠየቅ ይችላሉ።**

**ወይም**

አስተርጓሚ ከፈለጉ **በ 131 450 ወደ ቲስ/TIS ይደውሉ** እና ወደ የድጋፍ መስመራችን እንዲደውሉ ይጠይቋቸው።

አስተርጓሚ